## ኦሮሞ ፓለቲካና የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እጣ ፋንታ

## በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ ልብ ወለድ

## ክፍል ፯. ፩ የየእኛ ማስታወሻ፣ እናቴ በህይወት ካለሽ፣ ካለፈው የቀጠለ

የእኛ ማስታወሻዋን ይዛ ጠዋት በማለዳ ተነሳችና ከነአቶ ዳዲ ቤት ጓሮ ቁጭ ብላ ሌሊት ስለእናቷ ሁኔታ እያሰበች ሲያስጫንቃት ያደረውን የእናቷን ጤንነት እያሰበች ስሜቷን በማይላከው ደብዳቤ እንደሚከተለው አሰፈረችው።

ውድ እናቴ ምናልባት በህይወት ካለሽ የማዝነው ከእኔ የበለጠ ለአንች ውድ እናቴና ለቤተሰቦቸ ነው። አውቃለሁ፣ በየቀኑ ከዛሬ ነገ ልጀ ትመጣለች እያልሽ በር በር እያየሽ ተስፋ ሳትቆርጭ 10 ወር ሆነሽ። ልጅ የሚረገዘው ዘጠኝ ወር እንደሆነም አውቃለሁ። አንች ግን ዘጠኝ ወር አርግዘሽ በፅኑ ምጥ የተገላገልሻትን ልጅሽን በድጋሚ በጭንቅ አርግዘሽ ሳትገላገይ አስር ወር ሲያልፍሽ ምን እየተሰማሽ እንደሆነ እረዳለሁ። የእኔ የራሴ መከራ ሳያንሰኝ እናንተን ለዚህ መከራ መዳረጌ ሰላም ይነሳኛል። ያን ጊዜ ተማሪ እያለሁ ውሀ ልቀዳ ከጓደኞቸ ጋር ወጥቸ ትንሽ ከዘገየን እየተርበተበትሽ ፍለጋ ብቅ የምትይውን መቸም አረሳውም። ያን ጊዜ እኮ እናት ስለሆንሽ እንደው ስጊ ብልሽ ነው እንጅ የሚያሰጋ ነገር ብዙም አልነበረም።

እማ ሞተች ተብለሽ ቁርጥሽን አውቀሽ እርምሽን አውጥተሽ የልጆችሽ እናት ብትሆኝ ምኞቴ ነበር። እማ እመኝኝ የዘወትር ፀሎቴም ነው። እኔ በተአምር ተርፌ ቁሜ የምሄድ ብሆንም ያች የምታውቂኝ ጠንካራዋ፣ ባለተስፋዋ ልጅሽ አይደለሁም። ከሞቱት በላይ ካሉት በታች ያለሁ፤ ሞት እንደጥላ የሚከተለኝ ሰው ነኝ።

እማ ከእናንተ ከተለየሁ አፍ አውጥተው ለሰው የሚነግሩት ታሪክ ባይኖረኝም ጉድ ከእናት አይደበቅምና ጉዴን ልንገርሽ። እኔንም ነገዴንም ሀይማኖቴንም አጥብቆ በሚጠላ ባለጌ የኦሮሞ ጎረምሳ ተደፍሬ የጠላት ልጅ ፀንሸ ቆሽሸ ተቀምጫለሁ። አሁን አሁን ቀኑን እየቆጠረ ሆዴም እየሞላ ፅንሱም እየተንቀሳቀሰ ነው።  ፅንሱ በሆዴ ሲገላበጥ የሚሰማኝ በጣም የማልወደውና የሚያሳዝነኝ ሁለት አይነት ስሜት አለ።  አንዱ የማልወደው ስሜቴ እንዴት  በጣም ከሚጠላኝ፣ ማንነቴን ከሚጠየፍ ጨካኝ ሰው ልጅ እወልዳለሁ የሚል የሽብር ስሜት ሲሆን ሌላው የሚያሳዝን ስሜቴ ደግሞ በሆዴ ውስጥ ያለው ፅንስ ሳይፈልግ የመጣ የኔ የምስኪኗ የአማራ ተማሪ እጣ ፈንታ ለዚህ ያበቃው መከረኛ ነው ፣ እያልኩ ለፅንሱ አዝናለሁ።

እናቴ እርግዝናን ከመከራ ጋር አጣምሬ አየሁት። መቸም "ላይጠግን አይሰብር|" እንዲሉ አንድ ጥሩ ቤተሰብ እግዚአብሔር አምላክ ሰጥቶኛል። ሰውየው አቶ ዳዲ ይባላሉ፣ ባለቤታቸው ወይዘሮ ሌንሳና ልጃቸው ጫልቱ በጣም ጥሩ ሰዎች ናቸው። ጫልቱም ሁለት ልጆች አሏት።  እስከአሁን በህይወት ለመኖሬ እነሱ ብዙ አስተዋፅኦ አላቸው።

እማ የእኔን የእኔን ብቻ እየነገርኩሽ ስለጓደኞቸ ምንም ስላላልኩሽ የከዳኋቸው መሰለኝ። አብረውኝ ከታፈኑት ተማሪዎች አንድም ተማሪ አሁን ከጎኔ ባይኖርም መጀመሪያ አካባቢ አብረን ነበርን። አንድ የሚያደርገንና ያግባባን ነገር ቢኖር አፋኞቹ እኛን የሚጠሉን አማራና ኦርቶዶክስ ስለሆንን ብቻ ነውና ጠላቶቻችን በጋራ ስለሚጠሉን ነው። ጓደኞቸም ፈርዶባቸው እንደ እኔው በጣም ብዙ አሰቃቂ አደጋ ደርሶባቸዋል። እንደውም አንዳንዶቹን በህይወት መኖራቸውን እጠራጠራለሁ። የእነሱንም ወላጆች እግዚአብሔር ያበርታቸው።

እማ እናንተ አቅም የሌላችሁ ደካማ ገበሬዎች እንደሆናችሁ ይታወቃል። ልጆቻችሁን ረስታችሁ ተፅናንታችሁ ህይወት ባትቀጥሉም ዝም ካላላችሁ ሌሎቹንም እንዳታጡ እያሉ እንደሚያስፈራሩዋችሁ ሰምተናል። ከሁሉም የሚያሳዝነው እኛ የአማራ ተማሪዎች ተመርጠን ጥቃት ሲደርስብን የኢትዮጵያ ህዝብ ዝም ማለቱ ነው። ከዚህ ሁሉ የኢትዮጵያ ህዝብ እኛን ብሎ የሚጮኸው ሰው ቁጥር በጣም ጥቂት ነው። ሰሞኑን ከታፈንንና ከተሰወርን 10 ወር ሲሆነን እነመምህር ማአዛ ሙሀመድ አስበውን እንደዋሉ ሰማቸ አመሰገንኳቸው። እነሱ በፊትም ተከልክለው ነው እንጅ ሁሌም በልባቸው እንደሆን አውቄያለሁ።

ይኸን ሁሉ እንዴት ታውቂያለሽ እንደምትይ አውቃለሁ። ነገር ግን እነአቶ ዳዲ ራዲዮ እንዳዳምጥ ይፈቅዱልኛል። ለዚህ ነው አንዳንድ ነገር የምሰማው። ስልክ ደውየ እንዳነጋግራችሁም አንድ ሁለት ጊዜ ሞክረው ነበር። ነገር ግን ስልኬን ጥጋበኞቹ የኦሮሞ ጎረምሶች የነጠቁኝ ገና እንደያዙኝ ነው። እኔም በብዙ ጭንቅ ውስጥ ስላለፍኩ የአባባን ስልክ ቁጥር ረሳሁት መሰለኝ ወይም እሱ ስልክ ቁጥር ቀይሮ ሊሆን ይችላል መገናኘት አልቻልንም። ቢሆንልኝ የአንችን የውድ እናቴን ድምፅ ብሰማና እኔም አለሁ አታስቢ እናቴ ብየ ባረጋጋሽ አልጠላም ነበር። እኔን ረስተሽ በሰላም እንድትኖሪ እግዚአብሔር ይርዳሽ።

ዘውዲቱ የማነ
2020-10-02